የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19[th] Year No. 61
ADDIS ABABA 29[th] July, 2013

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፭ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ........................................ገጽ ፮ሺ፱፻፺

**አዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፭**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ማሻሻያ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፱ ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳፩) ተጨምሯል፡-

"፳፩/ የአካባቢና የደን ሚኒስቴር፡፡"

CONTENTS

Proclamation No. 803/2013

Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation ...... Page 6990

**PROCLAMATION No. 803/2013**

**A PROCLAMATION TO AMEND THE PROCLAMATION ON THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

WHEREAS, it has became necessary to amend the Proclamation on the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation No. 803/2013".

2. **Amendment**

The Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 is hereby amended as follows:

1/ the following new sub-article (21) is added under Article 9 of the Proclamation:

"21/the Ministry of Environment and Forest."

ያንዱ ዋጋ
Unit price 3.80

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፪/ በአዋጁና በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር" እና "የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር" የሚሉት ስያሜዎች ተሠርዘው እንደ ቅደም ተከተላቸው "የከተማ ልማት፣ የቤቶችና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር" እና "የውሃ፣ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስቴር" በሚሉት ስያሜዎች ተተክተዋል፤

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ረ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ረ) ተተክቷል፡-

"ረ) ዜጎች ከአቅማቸው ጋር የተመጣጠነ መኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ለተግባራዊነታቸውም ለክልሎች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፫፣ ፴፬፣ ፴፭፣ ፴፮፣ ፴፯ እና ፴፰ እንደ ቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፴፬፣ ፴፭፣ ፴፮፣ ፴፯፣ ፴፰ እና ፴፱ ሆነው የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፫ ተጨምሯል፡-

"፴፫. የአካባቢና የደን ሚኒስቴር

፩/ የአካባቢና የደን ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት የአካባቢ ደህንነት ዓላማዎችና በአካባቢ ፖሊሲው የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፤

ለ) በመንግሥትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ሥልቶች፣ ሕጎችና መርሐ ግብሮች ላይ የአካባቢ ተጽኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

ሐ) ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ፍትህን በሚያራምድና ከሚገኘው ጥቅም ትልቁን ድርሻ በእርምጃው ለሚነኩ ማህበረሰቦች በሚያስገኝ የስርየት እርምጃ ከደን ምንጣሮና ጉስቁልና ሊከተል ይችል የነበረውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት የመቀነሻ ሥርዓት ያዘጋጃል፤

2/ the designations "Ministry of Urban Development and Construction" and "Ministry of Water and Energy" appearing anywhere in the Proclamation and in other laws, currently in force, are deleted and replaced by the designations "Ministry of Urban Development, Housing and Construction" and "Ministry of Water, Irrigation and Energy", respectively;

3/ paragraph (f) of sub-article (1) of Article 25 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new paragraph (f):

"f) undertake studies for setting general directions for citizens to acquire residential houses compatible with their own means; provide capacity building support to regions for the implementation of same;"

4/ Articles 33, 34, 35, 36, 37 and 38 of the Proclamation are renumbered as Articles 34, 35, 36, 37, 38 and 39, respectively, and the following new Article 33 is added:

"33. The Ministry of Environment and Forest

1/ The Ministry of Environment and Forest shall have the powers and duties to:

a) coordinate measure to ensure that the environmental objectives provided under the Constitution and the basic principles set out in the environmental policy of Ethiopia are realized;

b) establish a system for environmental impact assessment of public and private projects, as well as social and economic development policies, strategies, laws and programmes;

c) prepare a mechanism that promotes social, economic and environmental justice and channel the major part of any benefit derived thereof to the affected communities to reduce emissions of greenhouse gases that would otherwise have resulted from deforestation and forest degradation;

መ) ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በየዘርፉና በየክልሉ ለመገንቢያ የሚውል ሃብት የሚያስገኙ ተግባራት ዝግጅትን ያስተባብራል፤ የአቅም ግንባታ ድጋፍንና የምክር አገልግሎትን ይሰጣል፤

ሠ) በአካባቢ ተፅኖ ግምገማ አዋጅ መሰረት ለልማት ፕሮጀክት የይሁንታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የፕሮጀክቱ ትግበራ በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅኖ በሚመለከተው የዘርፍ የፈቃድ ሰጪ አካል ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ተገምግሞ ውሣኔ የሚወስድበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

ረ) የተፈጥሮ ሃብቶች መሠረትን፣ በረሃ ማነትን፣ ደንን፣ አደገኛ ንጥረነገሮችንና የኢንዱስትሪ ዝቃጮችን እንዲሁም ሰው ሰራሽ የአካባቢ አደጋዎችን የሚመለከቱ በኢትዮጵያ የፀደቁ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶችን ድግግሞሽ፣ የሃብት ብክነት ወይም የእርምጃ ክፍተት ሳይፈጠር አቀናጅቶ የሚያስተገብር መርሐግብርን ያዘጋጃል፣ መመሪያዎችን ያወጣል፤ በየዘርፉና በየአስተዳደር እርከኑ መተግበራቸውንም ይከታተላል፤

ሰ) በዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር ላይ ይሳተፋል፣ እንደተገቢነቱም ስምምነቶቹ እንዲፀድቁ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሸ) ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ለመተግበር ተፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችን፣ ሕጎችንና መርሐ ግብሮችን እንደ ሁኔታው ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ሃሳብ ያመነጫል፣ አዘገጃጀታቸውን ያስተባብራል፤ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

d) coordinate actions on soliciting the resources required for building a climate resilient green economy in all sectors and at all governance levels as well as provide capacity building support and advisory services;

e) establish a system for the evaluation of the environmental impact assessment of investment projects submitted by their respective proponents by the concerned sectoral licensing organ or the concerned regional organ prior to granting a permission for their implementation in accordance with the Environmental Impact Assessment Proclamation;

f) prepare programmes and directives for the synergistic implementation and follow up of environmental agreements ratified by Ethiopia pertaining to the natural resources base, desertification, forests, hazardous chemicals, industrial wastes and anthropogenic environmental hazards with the objective of avoiding overlaps, wastage of resources and gaps during their implementation in all sectors and at all governance levels;

g) take part in the negotiations of international environmental agreements and, as appropriate, initiate a process of their ratification;

h) formulate or initiate and coordinate the formulation of policies, strategies, laws and programs to implement international environmental agreements to which Ethiopia is a party; and upon approval, ensure their implementation;

ኘ) የአገሪቱን የአካባቢና የደን እንዲሁም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በሚመለከት ዘገባን በየወቅቱ እያዘጋጀ ያሰራጫል፤

አ) መደበኛ ያልሆነ የአካባቢ ትምህርት መርሃ ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፣ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች መሠረት ደንን በሚመለከት ለግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለአካባቢና የደን ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡”

፭/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፮ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ረ) ተጨምሯል፡-

“ረ) የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/፲፱፻፺፭ ከአንቀጽ ፫ እስከ አንቀጽ ፲፫፡፡”

፮/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፯ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) ተጨምሯል፡-

“፲፩/በአዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/፲፱፻፺፭ ተቋቁሞ የነበረው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአካባቢና የደን ሚኒስቴር ተላልፈዋል፡፡”

## ፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

o) prepare and disseminate a periodic report on the state of the country's environment and forest as well as climate resilient green economy;

p) promote and provide non-formal environmental education programs, and cooperate with the competent organs with a view to integrating environmental concerns in the regular educational curricula.

2/ The powers and duties given to the Ministry of Agriculture, with respect to matters relating to forest, by the provisions of other laws currently in force, are hereby given to the Ministry of Environment and Forest."

5/ the following new paragraph (f) is added under sub-article (1) of Article 36 of the Proclamation (as re-numbered pursuant to sub-article (4) of this Article):

"f) from Article 3 to Article 13 of the Environmental Protection Organs Establishment Proclamation No. 295/2002."

6/ the following new sub-article (11) is added under Article 37 of the Proclamation (as re-numbered pursuant to sub-article (4) of this Article):

"11/The rights and obligations of the Environmental Protection Authority re-established under Proclamation No. 295/2002 are hereby transferred to the Ministry of Environment and Forest."

## 3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of July, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**